| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | *ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ሐተታ ፡ መጻሕፍት ። "* |
| ርእስ ፤ | *አንዱዓለም ፡ አራጌ ፤ "በዘመናት ፡ መካከል ፤ በእስር ፡ ቤት ፡ ጭንቅ ፡ ውስጥ ፡ የተወለዱ ፡ ሥራዎች ። "* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ።* |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥* ቍ.2011-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ሐተታ ፡ መጻሕፍት ።

Books Review | revue de livres | مراجعة الكتب

በቅርቡ ፡ ከደረሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡–

- **አንዱዓለም ፡ አራጌ** ፤ *"በዘመናት ፡ መካከል ፤ በእስር ፡ ቤት ፡ ጭንቅ ፡ ውስጥ ፡ የተወለዱ ፡ ሥራዎች ። "* ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 2010 ፡ ዓ.ም. ፤ 300 ፡ ገጾች ።

ኹላችን ፡ የምናውቃቸው ፥ የኹላችን ፡ ባለውለታ ፥ የነጻነት ፡ ታጋይ ፥ የስያሳ ፡ ሰው ፡ አንዱዓለም ፡ አራጌ ፥ ዛሬ ፥ ከብዙ ፡ ዓመት ፡ እስር ፡ ተፈትተው ፥ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትመውልናል ፤ እንኳን ፡ ለዚህ ፡ አበቃዎ! ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አለዎ! ፡ እንላቸዋለን ።




መጽሐፉ ፥ በትግል ፡ ሕይወት ፡ የሚደርሰውን ፡ አደጋ ፣ የሚፈጸመውን ፡ ግፍ ፣ የሚገጥመውን ፡ ፈተና ፣ የሚከፈለውን ፡ የመሥዋዕት ፡ ዋጋ ፡ ከመዝከር ፡ ከማስገንዘብ ፡ ጋራ ፥ በፈተና ፡ ያለፈ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የሚያገኘውንም ፡ ትምህርት ፡ ጭምር ፥ አላንዳች ፡ የቂም ፡ በቀል ፡ ስሜት ፥ በእውነተኛ ፡ የፈላስፋ ፡ ዐይን ፡ አይተው ፥ በተዋበ ፡ ዐማርኛ ፡ ደርሰውልናል ። የተለመዱ ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶች ፡ ቢኖሩበትም ፥ በጠቅላላው ፡ ደኅና ፡ የተናበበ ፡ ጽሑፍ ፡ በመኾኑ ፥ ንባቡ ፡ ይገራል ።

ድርሰቱ ፡ በስድ ፡ ንባብና ፡ በግጥም ፥ ባማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ መሰናሰሉ ፥ የመጽሐፉን ፡ አወቃቀርና ፡ አቀራረብ ፡ ከተለመደው ፡ ለየት ፡ ያደርገዋል ። ዐያሌ ፡ ትምህርት ፡ ይገኝበታልና ፥ ንባቡን ፡ እንመክራለን ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።